የሰ/መ/ቁ. 37742

ታህሣሥ 7 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጐስ ወልዱ

ሂሩት መሰሰ

አልማው ወሌ

ሱልጣን አባተማም

**አመልካች፡-** ወ/ሮ አልማዝ ጉንፋ ኦሪቲ ቀርቧል

**ተጠሪ፡-** ወ/ሮ ፀሐይ ሲበን የሺጥላ አለሙ ጠበቃ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ተወስኗል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የተመረመው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን የአሁን አመልካች የስር ጣልቃገብ አመልካች ሲሆኑ ተጠሪ የስር ከሳሽ ነበሩ፡፡ ጣልቃ ገብ አመልካች በአሁን ተጠሪ ላይ ባቀረቡት መቃወሚያ ተጠሪ ከሟች ጋር አብሬ ያፈራሁትን ቁጥሩ 373 የሆነውን ቤት ተከሣሾች ያካፍሉኝ ሲሉ ክስ ያቀረቡት እኔ በጣልቃ ገብ አመልካች (የአሁን አመልካች) ከሟች ባለቤቴ ከነበሩት አቶ ታምሩ አሸናፊ ጋር በባልና ሚስት የጋራ ንብረት በመሆኑና በመሐከላችን በተነሳው ያለመግባባት በፍ/ቤት ውሣኔ ስንለያይ ንብረቱ የጋራችን በመባሉ እኔ ለልጆቼ ስል ሳልካፈል ትቻለው(አልወሰድኩም) ነበር፡፡ ስለዚህ በመብቴ ላይ ውሳኔ ከመሰጠቱ በፊት ጣልቃ እንድገባ በማለት እንዲፈቀድላቸው ጠይቋል፡፡

የመጀመሪያ ደ/ፍ/ቤትም መዝገቡን በመመርመር በሰጠው ብይን የአሁን አመልካች የጣልቃ ልግባ አቤቱታቸው ላይ መሰረት ያደረጉት የሟች አቶ ታምሩ አሸናፊ ሚስት መሆናቸውን እና ከሳሽ (የአሁን ተጠሪ) ክስ ያነሱበት ቤት ከሟች ጋር አብረን ሰርተናል በማለት ነው፡፡ ይህ የጣልቃ ልግባ ምክንያት ደግሞ አመልካችን ጨምሮ(የስር ጣልቃ ልግባ ባይን) የአሁን ተጠሪና የሥር ሁለተኛ ተከሣሽ ክርክር ባነሱበት የመ/ቁ. 0057 ላይ የውርስ ንብረት አጣሪ ተሹሞ ሪፖርቱ የፀደቀበት ክርክር ነው ጣልቃ ልግባ ባይ በዚህ የጣልቃ ልግባ አቤቱታቸው በውርስ ንብረት አጣሪ ሪፖርት መሰረት ክርክር በተነሳበት የቤት ቁ. 373 ላይ ድርሻ አለኝ የሚል የጣልቃ ልግባ ምክንያት አላቀረቡም ይህ ከሆነ ደግሞ ከሣሽ ተጠሪ በውርስ አጣሪው ሪፖርት መሰረት በቤት ቁጥር 373 ላይ ክፍፍል ተደርጐ ድርሻዬ ይሰጠኝ ሲሉ ክስ ባቀረቡበት መዝገብ ላይ ጣልቃ ልግባ ባይ (አሁን አመልካች) በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 41/2/ መሰረት የጣልቃ ገብነታቸውን ማመልከቻ በክሱ ውስጥ ይገባኛል የሚሉብትን ምክንያት ሳይዘረዝሩና ሳይገልጹ ጣልቃ ልግባ ያሉት ጥያቄ ፍ/ቤቱ አልተቀበለውም ሲል ወስኗል፡፡

ይግባኝ ባይ(የአሁን አመልካች) በፍ/ቤቱ በተሰጠው ብይን ባለመስማማት ለፌደራል ከ/ፍ/ቤት ይግባኛቸውን አቅርቧል፡፡ ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን በማከራከር ጉዳዩን ከመረመረ በኋላ የተሰጠውን ብይን ጉድለት የለበትም በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 348/1/ መሰረት አጽንቷል፡፡

የሰበር አቤቱታም የቀረበው በዚሁ ውሣኔ ላይ ነው፡፡

አመልካች ግንቦት 4 ቀን 2000 ዓ.ም በፃፉት ማመልከቻ በፌ/የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የተሰጠው ውሣኔ እና በፌ/ከ/ፍ/ቤት የተሰጠው ውሣኔ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው በማለት አቤቱታ አቅርቧል፡፡

ይህ የሰበር ችሎትም አቤቱታውን መሰረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርቦ ክርክሩን ሰምቷል ጉዳዩ በሰበር ችሎት ቀርቦ እንዲታይ የተወሰነው አመልካች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 41 መሰረት ያቀረበችው የጣልቃ ልግባ ጥያቄ ውድቅ የተደረገበትን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ነው፡፡ በዚሁ መሰረት ይህን ነጥብ ግራ ቀኙ ወገኖች ከሰሙት ክርክር፣ አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከህጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

እኛም የዚህን ክርክር አመጣጥ በአጭሩ ስናየው ለአመልካች የጣልቃ ልግባ ምክንያት ከሟች ባለቤታቸው (አቶ ታምሩ አሸናፊ) ጋር በሚስትነት አብረው ያፈሩአቸው የጋራ ንብረት እንደነበረና ከሟች ጋር ያለመግባባት በመፈጠሩ ምክንያት በፍ/ቤት ተፋተው ንብረቱን በተመለከተ ለልጆቻቸው ጥቅም ሲሉ ሳይካፈሉት እንደቆየ እና የአሁን ተጠሪ በንብረቱ ላይ ውሳኔ እንዳያሰጡብኝ በማለት ነው፡፡

እንግዲህ ከዚህ መገንዘብ እንደቻልነው የአመልካች ጥያቄ ክርክር በተነሳበት ባለው ቤት ላይ መብት አለኝ የጋራ ንብረቱን እንደሚስትነቱ አልተካፈሉም እያሉ ነው አመልካች ከሟች ጋር ባልና ሚስት እንደነበሩ በፍ/ቤት እንደተፋቱ የተካደ ነገር የለም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 41 መሰረት ጣልቃ ገብቶ ለመከራከር ከጉዳዩ (ከክርክሩ) ጋር ተያያዝነት ባለው ጉዳይ መብትና ጥቅም እንዳለ ከተገለፀ ጣልቃ ለመግባት በቂ ምክንያት ነው በያዝነው ጉዳይም አመልካች የሟች ሚስት የነበሩ መሆናቸው ከመዝገቡ መረዳት ይቻላል፡፡ ሌላው የሥር ፍ/ቤት አመልካች በውርስ አጣሪው ሪፖርት ላይ ይህን ጥያቄ አላቀረቡም ብሏል ይህ ደግሞ የአመልካች በውርስ አጣሪው ሪፖርት ላይ ጥያቄ የለማቅረብ የጋራዬ ነው ባሉት ንብረት ላይ ጣልቃ ገብቶ ለመከራከር የሚከለክላቸው አይሆንም፡፡ ምክንያቱም ባለመብትነት የሚወሰነው ወደ ክርክር ከተገባና ግራ ቀኙ ከተከራከሩበት በኂላ ስለሆነ ነው፡፡

በመሆኑም የሥር ፍ/ቤት አመልካች በክሱ ውስጥ ያገባኛል የሚሉትን ምክንያት አልዘረዘሩም መብታቸውን አልገለፁም በማለት ጥያቄውን ውድቅ ማድረጉንና የከፍ/ቤቱም ይህን ማረም ሲገባው ማጽናቱ የሕግ ሥህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

## <u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌ/የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 16228 ጥቅምት 11 ቀን 2000 ዓ.የሰጠው ውሣኔ እና የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 61828 በመጋቢት 4 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽረዋል፡፡
2. አመልካች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 41 መሰረት ያቀረቡት ጥያቄ ተቀባይነት ያለው በመሆኑ ጣልቃ ገብተው ይከራከሩ ብለናል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. በፌ/የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የተጀመረው መዝገብ እንዲቀጥል በማድረግ የግራ ቀኙን ወገኖች ክርክር ከሰማ በኂላ በሕጉ መሰረት እንዲወሰን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 341 መሰረት መዝገቡን መልሰናል፡፡

4.ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ